የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ጥቅምት ፭፱ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 3
ADDIS ABABA, 9th November, 2023

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮/፪ሺ፲፭
የሕዝብን ሠላምና ደህንነት ለማስጠበቅ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ.....ገጽ ፲፭ሺ፪፻፵፱

Content

Proclamation No. 6/2023
State of Emergency Proclamation Issued to Protect Public Peace and Security Council of Ministers Proclamation…….....Page 15249

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፮/፪ሺ፲፭
የሕዝብን ሠላምና ደህንነት ለማስጠበቅ
የወጣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

መንግሥት የህዝብን ሰላም፣ የሀገር ደሕንነትን፣ እንዲሁም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትን የማስከበር ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመገንዘብ፤

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚታየውን በትጥቅ የተደገፈ ሕገወጥ እንቅስቃሴ በመደበኛ የሕግ ማስክበር ሥርዓት ለመቆጣጠር ወደማይቻልበት ደረጃ የተሸጋገረ በመሆኑ፤

ይህ እንቅስቃሴ የክልሉን ነዋሪ አጠቃላይ የግብርና፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ደረጃ ያወከ እና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ በመሆኑ፤

የሕዝብን ሠላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ እንዲሁም ሕግ እና ሥርዓት ለማስከበር የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

State of Emergency Proclamation No. 6/2023

STATE OF EMERGENCY PROCLAMATION ISSUED TO PROTECT PUBLIC PEACE AND SECURITY

WHEREAS, Cognizant of the responsibility of the Government to maintain public order, national security and constitutional order;

WHEREAS, the illegal militancy in the Amhara National Regional Government has reached a level at which it cannot be controlled using ordinary law enforcement mechanisms;

WHEREAS, this situation has disrupted the agricultural, economic and social activities of residents of the Region and presented a danger to the constitutional order;

WHEREAS, it has become necessary to take emergency measures to maintain public peace and safety and to uphold law and order;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፫ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት የሚከተለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጇል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሕዝብን ሠላምና ደህንነት ለማስጠበቅ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፭/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል፡-

፩/ **"የሕግ አስከባሪ አካል"** ማለት የሀገር መከላከያ ሠራዊት፣ የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የክልል ፖሊስ ኮሚሽን እና የአስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ የሚያሰማራቸው ሌሎች የፀጥታ አካላት ማለት ነው፤

፪/ **"የአስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ ዕዝ"** ማለት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፭ መሰረት የተቋቋመ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አደረጃጀት ማለት ነው፤

፫/ **"ሕግ"** ማለት የፌደራል ሕገ መንግሥት፣ እንደ አግባብነቱ በፌደራል ወይም በክልል መንግሥታት ሕግ አውጪ ወይም ሥልጣን ባለው ሕግ አስፈፃሚ አካል የወጣ የክልል ሕገ-መንግሥት፣ አዋጅ፣ ደንብ ወይም መመሪያ ማለት ነው፤

፬/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፤

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 93 Sub-Article 1 Paragraph (a) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby Proclaimed as follows.

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "State of Emergency Proclamation Issued to Protect Public Peace and Security Council of Ministers Proclamation No.6/2023".

2. Definition

For the purposes of this Proclamation:

1/ **"Law Enforcement Body"** means the National Defense Force, the National Intelligence and Security Service, the Federal Police Commission, the State Police Commission and other security agencies deployed by the State of Emergency Central Command.

2/ **"State of Emergency Central Command"** means a State of Emergency Central Command established pursuant to Article 5 of this Proclamation to enforce this State of Emergency;

3/ **"Law"** means the Federal Constitution or the State Constitution and, as the case may be, any Proclamation, Regulation or Directive of the Federal or State Legislature or competent executive body;

4/ **"Person"** means a natural or juridical person;

፫/ በዚህ አዋጅ በወንድ አነጋገር የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል፡፡

፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስተዳደር እንዲሁም በክልሉ አስተዳደር የሕዝብን ሠላምና ፀጥታ ለማስከበር የሚወሰድ እርምጃን፣ በክልሉ ወይም በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የፀጥታ ችግር የሚያባብስ ማንኛውንም እንቅስቃሴ ወይም ሁኔታን በሚመለከት እንደአስፈላጊነቱ በየትኛውም የሀገሪቱ አካባቢ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

<u>ክፍል ሁለት</u>
<u>ስለ አስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ ዕዝ</u>

፬. <u>የአስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ ዕዝ መቋቋም እና ኃላፊነት</u>

፩/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን የሚያስፈፅም በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጀነራል የሚመራ የአስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ ዕዝ ተቋቁሟል።

፪/ የአስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ ዕዙ አባላት፣ መዋቅር እና አደረጃጀት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚወሰን ይሆናል።

፫/ የአስቸኳይ ጊዜ መምሪያ ጠቅላይ ዕዙ ተጠሪነት ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር ይሆናል።

5/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall be applicable in the Amhara National Regional State and in any other part of the Country as necessary in connection with the need to take measures to maintain public peace and security or against activities or situations that exacerbate the Regional or National security condition in the Region.

<u>PART TWO</u>
<u>THE STATE OF EMERGENCY CENTRAL COMMAND</u>

4. <u>The Establishment and Responsibility of the State of Emergency Central Command</u>

1/ A State of Emergency Central Command, to be led by the Director General of the National Intelligence and Security Service, entrusted with the responsibility to implement the state of emergency Proclamation is hereby established.

2/ The Prime Minister shall determine the membership, structure, and organization of the State of Emergency Central Command.

3/ The State of Emergency Central Command shall be responsible to the Prime Minister.

፬/ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ጠቅላይ መምሪያ ዕዙ፡-

ሀ) አግባብነት ካላቸው አካላት የተወጣጡ እና በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ኃላፊነት ወስደው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ተፈፃሚ የሚያደርጉ ግብረሃይሎችን ወይም ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፣

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተመለከቱ እርምጃዎችን በተመለከተ አስፈላጊውን ውሳኔ ያስተላልፋል፣ ያስፈፅማል፣

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተመለከቱ የተከለከሉ ተግባራት እና ግዴታዎችን ያስከብራል፣

መ) በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሚገኙ የሕግ አስከባሪ አካላትን በአንድ ዕዝ ሥር አድርጎ በላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣

ሠ) ኃላፊነቱን ለመወጣት ሌሎች አስፈላጊ እና አግባብ የሆኑ ሥልጣኖች ይኖሩታል።

ክፍል ሶስት
በአስቸኳይ ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎችና የተከለከሉ ተግባራት

፭. በአስቸኳይ ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎች

የአስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ ዕዙ የዚህን አዋጅ ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን፡-

፩/ የአደባባይ ስብሰባና ሰልፍ ማድረግ፣ መደራጀት፣ በቡድን ሆኖ መንቀሳቀስን የመከልከል፣

፪/ የሰዓት እላፊ የማወጅ፣ ለተወሰነ ጊዜ አንድ መንገድ፣ አገልግሎት መስጫ ተቋም መጓጓዣ ዘዴ እንዲዘጋ እና እንዲቋረጥ ለማዘዝ፣

4/ The State of Emergency Central Command:

a) may set up task forces or committees that are composed from relevant bodies and take responsibility for the implementation of various aspects of the State of Emergency Proclamation,

b) it shall pass and enforce decisions necessary in relation to Article (5) of this Proclamation,

c) shall enforce Article (6) of this Proclamation,

d) coordinate, direct and oversee law enforcement entities in the Amhara National Regional state under a unified command structure,

e) shall have other necessary and appropriate powers to discharge its responsibilities.

PART THREE
MEASURES TO BE TAKEN AND PROHIBITED ACTIONS DURING STATE OF EMERGENCY

5. State of Emergency Measures

When the State of Emergency Central Command believes that it is necessary to achieve the purpose of this Proclamation, it has the authority to:

1/ Prohibit public assembly, demonstration, association or group activities,

2/ Declare a curfew; order the closure of roads, service providing institution or transportation system for a limited period of time,

፫/ ሰዎች ለጊዜው በተወሰነ ቦታ እንዲቆዩ፣ ወደ ተወሰነ አካባቢ እንዳይገቡ ወይም ከተወሰነ ቦታ እንዲለቁ ለማዘዝ፣

3/ Give orders for persons to stay in a certain place, impose bans on entry into or order evacuation from a given place,

፬/ የጦር መሳሪያ፣ ስለት ወይም አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮችን ይዞ መንቀሳቀስን ለመከልከል፣

4/ Prohibit the carrying of firearms, blades or dangerous objects,

፭/ በሀገረ መንግሥቱ እና በሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱ ላይ የሚቃጡ ወንጀሎችን እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመጣስ እና አፈፃፀሙን የማደናቀፍ ወንጀልን መፈፀሙ፣ መሞከሩ ወይም ለመፈፀም በዝግጅት ላይ መሆኑ የተጠረጠረ ማናቸውንም ሰው ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ በቁጥጥር ሥር በማድረግ ለማቆየት፣

5/ Detain anyone suspected of committing, attempting or preparing to commit crimes against the state and the constitutional order or violating the State of Emergency Proclamation or obstructing its implementation without a court order,

፮/ ወንጀል እንደተፈፀመባቸውን ወይም ሊፈፀምባቸው እንደሚችል የተጠረጠሩ እቃዎችን ለመያዝ ሲባል ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በየትኛውም ጊዜ ማናቸውንም ሥፍራ እና መጓጓዣ ለመበርበር፣

6/ Without a court warrant, search any place at any time to seize items used or that may be used to perpetrate a crime,

፯/ መንግሥታዊ እና ህዝባዊ ተቋማትና የመሠረተ ልማቶች ጥበቃ ሁኔታን ለመወሰን፣

7/ Determine the modality for the protection of governmental and public institutions and infrastructures,

፰/ ማናቸውም ከዚህ አዋጅ ዓላማ በተፃረረ መልኩ እየተነቀሳቀሱ እንደሆነ የተጠረጠሩ የመገናኛ ብዙሐንም ሆነ ሌሎች አካላት እንዲዘጉ፣ እንዲቋረጡ፣ ፈቃዳቸው እንዲሰረዝ ወይም እንቅስቃሴያቸው እንዲገደብ ለማዘዝ፣

8/ Order the closer, termination or revocation of the license or impose any restriction on any media outlet or other entity suspected of acting contrary to the purpose of this proclamation,

፱/ ማንኛውም አገልግሎት መስጫ ተቋም እንዳይዘጋ እና ለሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማዘዝ፣

9/ Order that any service providing institutions stay open and be available for public use or service,

፲/ ማንኛውም የህዝብ ትራንስፖርት መስጫ ተሽከርካሪዎች እና ማንጓጓዣ እቃዎች አገልግሎት እንዲሰጡ ለማዘዝ፣

10/ Order any public transport vehicles and conveyances to provide services,

፲፩/ የተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች እና መዋቅሮችን መልሶ ማቋቋም፣ ማደራጀት ወይም የአስተዳደር እና የፀጥታ ጉዳዮችን በተመለከተ ውሳኔዎችን የማስተላለፍ እና ሌሎች እርምጃዎችን የመውሰድ፣

፲፪/ የሕዝብን ሰላም፣ የሀገር ደህንነትን አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን የመወሰድ፣ ውሳኔዎችን የማስተላለፍ እና ትእዛዝ የመስጠት ሥልጣን አለው።

11/ Reorganize or reestablish administrative structures or decide and take measures on administrative and security matters,

12/ Take measures, adopt decisions and issue orders necessary to protect public peace and national security.

፮. <u>የተከለከሉ ተግባራት እና ግዴታዎች</u>

፩/ ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ፣ በአዋጁ መሰረት የሚወጡ መመሪያዎችን፣ የሚሰጡ ትዕዛዞች እና የሚተላለፉ ውሳኔዎችን የመተግበር እና የማክበር ግዴታ አለበት።

፪/ የአስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ ዕዙን እንቅስቃሴ እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አላማ የሚቃረን፣ የሚቃወም እና በክልሉ የአመጽ እንቅስቃሴን የሚያበረታታ፣ ሰላማዊ ዜጎችን የሚያሸብር፣ እንዲሁም የፀጥታ መደፍረሱን የሚያባብስ ንግግር፣ የቀጥታም ሆነ የተዘዋዋሪ ቅስቀሳ በማንኛውም መንገድ ማድረግ ወይም ማሰራጭት የተከለከለ ነው።

፫/ በየትኛውም መንገድ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለታጣቂ ቡድኖች የገንዘብ፣ የመረጃ፣ የቁስም ሆነ የሞራል ድጋፍ ማድረግ የተከለከለ ነው።

፬/ ከአስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ ዕዙ ፈቃድ ውጪ ማንኛውንም የአደባባይ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ የተከለከለ ነው።

፭/ ከአስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ ዕዙ ፈቃድ ውጭ ማናቸውንም የጦር መሳርያ ይዞ መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው።

6. <u>Prohibitions and Obligations</u>

1/ Everyone has a duty to implement and comply with this Proclamation, Regulation Directives and orders to be issued in accordance with the Proclamation.

2/ It is prohibited to make or disseminate any speech, engage in direct or indirect incitement that obstructs the activities of the State of Emergency Central Command and undermines the purpose of this Proclamation or that encourages violence and insurrection or terrorizes peaceful citizens, and exacerbates insecurity.

3/ It is prohibited to directly or indirectly supply armed groups with money, information, material, or moral support;

4/ It is prohibited to hold public meetings or demonstrations without the permission of the State of Emergency Central Command.

5/ It is prohibited to carry any weapon without the permission of the State of Emergency Central Command.

፮/ ማንኛውንም ወሳኝ በሆነ የአገልግሎት ዘርፍም ሆነ በምርት ሂደት ላይ የስራ ማስተጓጎል ወይም የኢኮኖሚ አሻጥር መፈፀም የተከለከለ ነው።

፯/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን አፈፃፀም ሰበብ በማድረግ የግል ጥቅም ለማግኘት ስልጣንን አላግባብ መጠቀም፣ ምክንያታዊ የሆነ ጥርጣሬ ሳይኖር ሆን ብሎ ዜጎችን ማሰር ወይም መሰል እርምጃ መውሰድ በጥብቅ የተከለከለ ነው።

፯. <u>ተመጣጣኝ ኃይል ስለመጠቀም እና የማይታገዱ መብቶች</u>

፩/ የአስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ ዕዝ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃዎችን ለማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሕግ አስከባሪ አካላት ተመጣጣኝ ኃይል እንዲጠቀሙ መመሪያ ለመስጠት ይችላል።

፪/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መምሪያ ዕዝ በሚያወጣቸው መመሪያዎችም፣ በሚወስናቸው ውሳኔዎች እና በሚወስዳቸው እርምጃዎች በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ ፺፫ ንዑስ አንቀጽ ፬ ፊደል ተራ (ሐ) መሠረት ሊታገዱ የማይችሉ የሕገ መንግሥት ድንጋጌዎችን እና መብቶችን፣ እንዲሁም የተመጣጣኝነትን እና የአስፈላጊነት መርሆዎችን ማክበር ይኖርበታል።

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፰. <u>ተፈፃሚነታቸው የታገዱ ሕጎች</u>

፩/ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ እሲኪጠናቀቅ ድረስ በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፱) ከተገለፀው አግባብ ውጪ የትኛውም የዳኝነት አካል ሥልጣን አይኖረውም።

6/ It is prohibited to disrupt work or engage in economic sabotage in any critical service sector or production process.

7/ It is strictly prohibited to abuse power for personal gain under the pretext of the implementation of the emergency decree, to deliberately detain individuals without reasonable suspicion or engage in such abusive conduct.

7. <u>The Use of Proportional Force and Non-Derogable Rights</u>

1/ The State of Emergency Central Command, when deemed necessary, can order law enforcement agencies to use proportional force to implement the emergency measures referred in this Proclamation.

2/ The Directives, decisions and the measures taken by the State of Emergency Central Command shall be in accordance with the Article 93 Sub-Article 4 Paragraph (C) of the Constitution, and principles of proportionality and necessity.

<u>PART FOUR</u>

<u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

8. <u>Suspended Laws</u>

1/ No judicial organ shall have jurisdiction regarding matters covered by this Proclamation until the end of the State of Emergency period except in accordance with Article (9) of this Article.

፪/ በቪዬና ኮንቬንሽን፣ በሌሎች የዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ደንቦች እውቅና የተሰጣቸው የዲፕሎማቲክ መብቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ የፍሬ ነገርና የሥነ ሥርዓት ሕጎች ይህ አዋጅ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ተፈፃሚነታቸው ታግዶ ይቆያል።

2/ Without prejudice to the diplomatic immunities and privileges recognized under the Vienna Convention and other pertinent treaties to which Ethiopia is a party to as well as under customary International Law, the application of substantive and procedural laws inconsistent with this Proclamation shall remain suspended for the duration of this Proclamation.

፱. <u>የወንጀል ተጠያቂነት</u>

9. <u>Criminal Liability</u>

፩/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በአዋጁ መሰረት የወጡ መመሪያዎችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም እንደጥፋቱ ክብደት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

1/ Whosoever violates the provisions of this Proclamation, subsequent Regulations and Directives is punishable with simple imprisonment not exceeding Three Years, or when the fault is grave, the punishment shall be rigorous imprisonment up to Ten Years.

፪/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በአዋጁ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ የተፈፀመው ወንጀል በሌሎች ሕጎች ከዚህ ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስከትል ከሆነ የከበደው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆናል።

2/ If other laws provide a higher penalty for conduct that constitutes a violation of the provisions of this Proclamation, subsequent Regulations and Directives; the higher penalty shall be applicable.

፫/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ወቅት የተፈፀሙ የአዋጁ እና በአዋጁ ማዕቀፍ የሚወጡ ደንብ እና መመሪያ ጥሰቶች የሚያስከትሉት የወንጀል ተጠያቂነትን በተመለከተ የአዋጁ ተፈጻሚነት ጊዜ ቢያበቃም በኢፌድሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የወንጀል ክስ ሊቀርብ ይችላል።

3/ Criminal charges could be pressed in accordance with Article 9 Sub-Article 2 of the Criminal Code with regard to criminal liability arising out of violations of this Proclamation or Regulations and Directives issued pursuant to the Proclamation.

፬/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በአዋጁ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ የሚመጣ የወንጀል ተጠያቂነትን አስመልክቶ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ መደበኛ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎችም ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

4/ Procedural rules of the regular criminal justice system that in contravention with this Proclamation shall not be applicable with regard to criminal liability arising out of violations of this Proclamation or Regulations and Directives issued pursuant to this Proclamation.

፭/ የፀጥታ ሁኔታው የመደበኛ የዳኝነት እና የፍትሕ አካላት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በማያስችልበት ሁኔታ ውስጥ ባሉ አካባቢዎች ከዚህ አዋጅ ጥሰት ጋር ተያያዥ የሆኑ የወንጀል ጉዳዮችን አስመልክቶ የወታደራዊ ፍርድ ቤቶች እና የፍትሕ አካላት መደበኛ የዳኝነት እና የፍትሕ አካላትን ተክተው እንዲሰሩ የአስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ ዕዝ ሊወስን ይችላል።

5/ In circumstances where the security situation does not allow the formal judicial organs to discharge their responsibilities, the State of Emergency Central Command may authorize military courts and judicial organs to handle criminal cases related to violations of this Proclamation in lieu of ordinary courts and judicial organs.

፲. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሀገርን ሰላምና ህልውና፣ የሕዝብን ደህንነት፣ ሕግ እና ሥርዓትን ለማስከበር በህገ መንግሥቱ አንቀፅ ፺፫ ንዑስ አንቀጽ ፬ ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት ድንብ የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል።

፪/ የአስቸኳይ ጊዜ ጠቅላይ መምሪያ ዕዙ በአዋጁ፣ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በሚወጡ ደንቦች የተሰጠውን ስልጣን ተግባራዊ ለማድረግ እና ሃላፊነቱን ለመወጣት አስፈላጊ መመሪያዎችን ያወጣል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚወጡ መመሪያዎች ተፈፃሚ ከመደረጋቸው በፊት ለህዝብ በስፋት ተደራሽ በሆኑ የመገናኛ ብዙሐን ለሕዝብ እንዲተዋወቁ መደረግ ይኖርበታል።

10. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers has the power to issue Regulations to safeguard peace, national security, public safety and uphold law and order in accordance with Article 93 Sub-Article (4) Paragraph (a) of the Constitution.

2/ The State of Emergency Central Command shall issue necessary Directives for the implementation of the powers and responsibilities given to it by this Proclamation and Regulations to be issued under this Proclamation pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

2/ The Directives issued according to Sub-Article (2) of this Article shall be communicated to the public through media outlets that are widely accessible to the public before they are implemented.

፲፩. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

፩/ ይህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከታወጀበት ጊዜ ጀምሮ ለስድስት ወራት የጸና ይሆናል።

፪/ የስድስት ወር ጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ በፊት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአዋጁ ተፈፃሚነት ቀሪ የሚሆንበትን ጊዜ ሊወስን ይችላል።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

ዐብይ አህመድ ዓሊ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

11. <u>Effective Date</u>

1/ This State of Emergency Proclamation shall remain in effect for six months starting from the time it is promulgated by the Council of Ministers.

2/ The House of People's Representatives can terminate the Proclamation before the end of the six-month period.

Done at Addis Ababa on this 9th Day of November, 2023.

ABIY AHMED ALI (DR.)
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA